# የኢህአዴግ ኑዛዜ ወይንስ የለውጥ አቅጣጫ?

## ---አማራጩ ሕዝብን የስልጣኑ ባለቤት ማድረግ ብቻ ነው--

**አክሎግ ቢራራ (ዶር)**

በህወሓት የበላይነት የሚገዛው የኢህአዴግ የስራ አስኪያጅና አስፈጻሚ ኮሚቴ፤ የሕዝብን ባጀት ተጠቅሞ፤ ለሶስት ሳምንታት ያህል የኢትዮጵያን ሕዝብ ችግሮች ካላዘነ በኋላ መግለጫ አውጥቶ ሕዝብን እያነጋገረ ነው። ይህ የምስጢር ጉባኤ የተካሄደው የህወሓት የስራ አስፈጻሚ ቡድን ለሳምንታት በመቀሌ የዝግ ችሎት አድርጎ ራሱን በአዲስ መልክ አወቃቅሬአለሁ ካለ በኋላ ነው። ቡድኑ አጠናክሮ የወጣው አሁንም ራሱን የስልጣን መአከል አድርጎ እንዴት የበላይ ሆኘ እገዛለሁ በሚል የህወሓቶችን ቀጣይነት የሚያሳይ ስልት መሆኑን ማስታወስ አስፈላጊ ነው። የኢህአዴግ አመራር ክብደት የሰጠው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ስልጣን ሳይሆን ለአዲሱ የህወሓት አመራር የበላይነት መሆኑ በግልጽ ይታያል።

ኢህአዴግ፤ ሕዝብን ላስቆጡትና ለአስነሱት፤ ለእልቂቶች፤ ለፖለቲካ እስረኞች፤ ለፍልሰቶች፤ ለስደት፤ ለአገሪቱ በውጭ ኃይሎች መከበብ፤ ለማህበረሰባዊና ለሰብ አዊ መብቶች መታፈን፤ ለኑሮ ውድነት፤ ለፍጽሙ ድህነት፤ ለስራ አጥነት፤ ለሕዝብ የፖለቲካ ስልጣን አለመኖር ወዘተ ምንም አይነት አጥጋቢ መልስ አልተሰጠም። The root causes that prompted popular resistance for the past two years remain intact. ችግሮቹ ካልተፈቱ በስተቀር ሕዝባዊው አመጽ በኃይል ቢታፈንም አያቆምም።

ችግሮቹን የፈጠረው የኢህአዴግ አመራር ራሱ ነው። የፈጠረውን ችግር ራሱ ፈትሾና ተችቶ ራሱ ሊፈታቸው አይችልም። የፍላጎት አለመኖር ክፍተት ብቻ ሳይሆን አቅምና ጥበብ ይጎድለዋል።

ብዙ የአገር ውስጥና የውጭ ተመልካቾች ተስፋ አድርገውት የነበረው ሂደት፤ የኢህአዴግ የስራ አስኪያጅና ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ፤ በመላው ኢትዮጵያ የተከሰተውን ህውከት፤ የእርስ በርስ ግጭት፤ የንጹሃን ዜጎች እልቂት፤ የንብረት መውደም ተመልክቶ የሕዝብን እሮሮ ይሰማል፤ ከሕዝብ ጋር፤ ከተቃዋሚ ፓርቲዎች ጋር፤ ከምሁራንና ከሌሎች ማህበረሰባዊ ክፍሎች ጋር በመከካር፤ **<u>የጋራችን የሆነችውን ኢትዮጵያን</u>** ከመፈራረስና ሕዝቧን ከእርስ በርስ እልቂት ሊታደግ ይሞክራል የሚል ተስፋና ምኞት ነበር። አስተማማኝ ሁኔታዎችን ለመፍጠር የፖለቲካ እስረኞችን ይፈታል የሚል ተስፋ ነበር። የጸረ-ሽብርተኛውን አዋጅ ይሰበዋል፤ ቢያንስ ያሻሽለዋል የሚል ተስፋም ነበር ወዘተ፤ ወዘተ።

ገዢው ፓርቲ ኢህአዲግ፤ የኢህአዲግ ስራ አስፈፃሚ ስብሰባውን ሲጀምር "ወሳኝ ውሳኔዎች ይተላለፉበታል ብሎ" የኢትዮጵያን ሕዝብ ለማዘናጋት ሞክሮ ነበር። አንድ ሰዓት የፈጀውን መግለጫ ሳዳምጥ ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ ምን ብሎ ኢህአዴግን ይተቸው ይሆን? ከማለት ውጭ የኢትዮጵያን 105 ሚሊየን ሕዝብ ተስፋ የሚሰጥ፤ የሕዝብን አመኔታ የሚያረጋግጥ፤ ኢትዮጵያን ወደ ተሻለ አቅጣጫ የሚያስኬድ አላየሁም፤ አልሰማሁም። በእኔ እምነት፤ ይህ መግለጫ ያጠናከረው የህወሓትን የበላይነትና ቀጣይነት ነው ለማስባል የሚያስችሉ ሁኔታዎች አሉ። ፋይዳ ቢስ መሆኑ ነው። አሁንም በሕዝብ ስም የሚነግዱት ኃይሎች የበላይነቱን ይዘዋል።

አንድ፤ "ኢህአዴግ የአመለካከትና የተግባር አንድነት ፈጥሯል" ሲባል የነበሩት ብሄር ተኮር የፖለቲካ ፓርቲዎችና መሪዎቻቸው አሁንም ባለፉት 26 ሕዝብን አፍነው የገዙበት ጸረ-ሕዝብ፤ ጸረ-ዲሞክራሲ አገዛዝ ወደፊትም እንዲቀጥል ተስማምተናል ከሚለው በምንም አይለይም።

ሁለት፤ የአመለካከት አንድነት አለ ማለት በጥቂቶች፤ ለጥቂቶች መሳርያ የሆነው የመንግሥት ስርዓት ያለምንም መሰረታዊ ለውጥ እንዲቀጥል ወስነናል ከሚለው አይለይም።

ሶስት፤ ኢህአዴግ ያወጣው መግለጫ ማዘናጊያ ነው። "ይቅርታ" ብሎ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለማዘናጋት ሞክሯል። ፈረንጆችን፤ በተለይ የአሜሪካን መንግሥት ይኼው "ይቅርታ" ጠይቄአለሁ፤ የፖለቲካና የማህበረሰብ ምህዳሩን ለማስፋት "ቃል ገብቻለሁ፤ መድብለ ፓርቲ እቀበላለሁ" በሚል ስልት የሚደረግበትን የውጭ ጫና ለመወጣት ሞክሯል።

አራት፤ በመግለጫው ላይ እንደተናገረው፤ ኢህአዴግ ኦሮሞውን ሆነ አማራውን፤ አፏኩን ሆነ ሶማሌውን እየመረጠ መቀጣጫ እንደሚያደርግ ወስኗል።

አምስት፤ ደርግ የሚቀጣውን ግለሰብ በግልጽ "የፍየል ወጠጤ" በሚል የፉከራ ዘፈን ይገድል ነበር። ህወሓት የሚገድለው በድብቅና በምስጢር ነው፤ አብዛኛውን በሌሎች እያመካኘ። በምንም የማይቀረው እልቂት በሚቀጥሉት ወራት ብዙ ንጹህ ወገኖቻችን ሰለባ ይሆናሉ። ሌላው ቀርቶ ከደቡብ ወደ ትግራይ ስኳር እንዳይተላለፍ ያደረጉ ግለሰቦች ቅጣት ይጠብቃቸዋል። ይህ ሁሉ የሚደረገው ሰላምና እርጋታ እንዲኖር በሚል ስልት ይሆናል።

ስድስት፤ የህወሓት የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይነት ውሳኔ ስኬታማ የሚሆነው በደህንነት፤ በፌደራል ፖሊስና በመከላከያ ኃይል ይሆናል ማለት ነው። ለምሳሌ፤ ሰላማዊ ሰልፍ እንዳይካሄድ መወሰኑ ከህወሓቶች ግንዛቤና ድምዳሜ የተለየ አይደለም። ስታንደርድ የተባለው ጋዜጣ ያወጣውን ሰነድ መልሶ ማየት ተገቢ ነው።

አዲሱን የኢህአዴግን መግለጫ የማየው ልክ የአስቸኳይ አዋጁን በሚመስል መልኩ እንደታወጀ መመሪያ ነው። መግለጫው እንዲህ ይላል።

" ....መንገድ መዝጋት አይቻልም፣ የግል እና የመንግስት ሚዲያዎች ህዝብን የሚያጋጭ መልዕክት ማስተላለፍ አይችሉም፣ የተፈናቀሉትን መልሰን እናቋቁማለን፣ ከዚህ በኋላም መፈናቀል እንዳይኖር ጠንክረን እንሰራለን፣ -ለኢትዮጵያ ህዝብ የተፋጠነ አገልግሎት ለመስጠት መልሰን የሚናዋቅራቸው መስሪያ ቤቶች ይኖራሉ፣ እስከ አሁን ለበደልንህ በደል ኢህአዲግ ተጠያቅ ነው።ይቅርታም እንጠይቃለን....." መብቶችን ፍጹምና ጭካኔ በተሞላበት መልክ ገፏቸዋል። የሚቀጡት የበላይ ባለሥልጣናት አጥፊዎች አይሆኑም። መቀጣጫ የሚሆኑት በየፓርቲውና በየክልሉ የሚገኙ ተቃዋሚ ግለሰቦች ይሆናሉ።

የተበላሸውና በሙስና የገማው አስተዳደር በተዓምር ይለወጣል የሚል እምነት የለኝም። “አሳ የሚገማው ከራሱ ስለሆነ” አፋኙ፤ ጠባብ ብሄርተኛውና ሙሰኛው አካል እንዳለ ሆኖ መልካም አስተዳደር ሊኖር አይችልም። ስለዚህ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ወደ ባሰ ችግር ተሸጋገረ ማለት ነው።

የዚህ መግለጫ መንስኤ ምንና ማን እንደሆነ ወደፊት ግልጽ መሆኑ አይቀርም። እኔንና ሌሎችን ተመልካቾች ያሳሰበው በኢህአዴግ ውስጥ፤ በአንድ በኩል በህወሓት የትግራይን ሕዝብ እወክላለሁ በሚለው፤ በሌላ በኩል የኦሮሞውንና የአማራውን ሕዝብ እንወክላለን በሚሉት በኦህዴድና በብአዴን መሪዎች የተነሱት መሰረታዊና አግባብ ያላቸው ጥያቄዎችና ልዩነቶች ለምን የውሃ ሽታ ሆኑ? የሚለው ጭምር ነው። ሕዝብ የጠየቀውና የሚጠይቀው አስኳል ጉዳይ የፖለቲካውንና የኢኮኖሚውን አንበሳ ክፍል የያዘው ህወሓት ስለሆነ፤ ይህ የበላይነት ሊቀጥል አይችልም፤ መለወጥ አለበት የሚል ነው።

የኦህዴድና የብአዴን መሪዎች ለሕዝብ ፍትህ-ርትህ፤ ስልጣን፤ የሕግ የበላይነትና ዲሞክራሲ የተስፋ ጭላንጭል ከሰጡ በኋላ፤ ቃላቸውን ሰበው አሁን የወጣውን **የህወሓትን ጫና** የሚያሳይ መግለጫ ሙሉ በሙሉ ከተቀበሉ ለሚወክሉት ሕዝብ ሌላ መግለጫ ማቅረብ ግዴታቸው ነው።  አለያ፤ ታሪክ ይታዘባቸዋል።

በእኔ እምነት በኦህዴድና በብአዴን በኩል ሆነው ለመሰረታዊ ለውጥ የሚሟገቱ ግለሰቦችና ቡድኖች የጀመሩትን ትግል መቀጠል ግዴታቸው ነው። ይህ ሕዝብን የሚያጓጓ የመሰረታዊና የዲሞክራሳዊ አቅጣጫዎችን የሚያመለክት የለውጥ ትግል ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊያን የሚፈልጉትና የሚመኙት ሆኖ አየዋለሁ። የኢህአዴግን መግለጫ ረጋ ብሎ ለሚመለከተው በኢህአዴግ ውስጥ እስካሁን የህወሓት አገልጋዮችና አስተጋቢዎች ሆነው የቆዩት ፓርቲዎችና “መሪዎች” ራሳቸውን ከህወሓት መንጋጋ “ነጻ” አውጥተናል፤ “አሽከሮችና ሎሌዎች አይደለንም” ለማለት የሚችሉት የጀመሩትን ክርክር ሲቀጥሉና ከሕዝቡ ጎን ሲቆሙ ብቻ ነው። ሕዝብን ከመረጡ ማንም ኃይል ሊያጠቃቸው አይችልም። በአገር ቤትና በውጭ የምንኖር ተቆርቋሪዎች ታሪካዊ ኃላፊነት ለለውጥ የሚታገሉትን፤ በተለይ የኦሮሞውንና የአማራውን ሕዝብ ጭኸት እንደ ራሳቸው ጭኸት አድርገው የሚታገሉትን ክፍሎች መደገፍ ነው።

ችግሩ በኢህአዴግ መግለጫና አዋጅ አይፈታም ያልኩበትን ምክንያቶች በአጭሩ ላቅርብ፤

አንድ፤ ሕዝቡ ከልቡ ህወሓት/ኢህአዴግን አልቀበልም ብሎ “ሸፍቷል”። የህወሓትን በትር ከመፍራት ይልቅ የሕዝብን አመኔታ፤ ፍቅርና አድናቆት መሸመት ይበልጣል።

ሁለት፤ መሰረታዊ ለውጦችን የሚፈልጉ፤ በተለይ በኦህዴድና በብአዴን ውስጥ የሚታገሉ መሰረታዊ ለውጥ ፈላጊዎች አደጋ እንደሚደርባቸው መገመትና መዘጋጀት ይኖርባቸዋል።

ሶስት፤ ለዚህ የሚጠቅመው ሕዝቡን መቀስቀስ፤ አይዞህ ማለት፤ በደህንነት፤ በፌደራል፤ በክልል ውስጥ፤ በፌደራል ደረጃ በመከላከያ ኃይሉ የሚያገግሉት አባላትን ከሕዝብ ጎን እንዲቆሙ ተከታታይ ቅስቀሳ ማድረግ ነው።

አራት፤ ወጣቱ ትውልድ “ወያኔ በቃ፤ ወያኔን አንፈልግም” ብሎ መስዋእት ከፍሏል። ከወጣቱ ትውልድ ጋር አብሮ የቆመን ኃይል ማንም ሊያፍነውም፤ ሊጨፈጭፈው አይችልም። ይህ ሲባል የሚገደልና የሚታሰር አይኖርም ማለቴ አይደለም። ኢህአዴግ ሰላማዊ ሰልፎችን ከልክሏል። ወጣቱ ከተንቀሳቀሰ ግድያ አይቀርም ማለት ነው። ይህ ከሆነ ከመቸውም በባሰ ደረጃ ሁኔታው ይባባስል። ኢህአዴግ ይፈርሳል። ትላንት ያወጣውን መግለጫ ስቦ ሌላ መግለጫ እንዲያወጣ ይገደዳል።

አምስት፤ ይህን የመሰለ፤ መሰረታዊ ችግሮችን ከመፍታት ይልቅ፤ ራስን የማዳን ሙከራ በተከታታይ የኢትዮጵያ መንግሥታት--በአጼ ኃይለ ሥላሴ፤ በደርግና አሁን በኢህ አዴግ ተሞክሯል። የችግሩ መሰረት አገዛዙ የፈጠረው መሆኑ ግን ተነክቶ አያውቅም። የሕዝብን መብት የነፈገ መንግሥት ምን ጊዜም “ጉልቾች **ቢቀያይር” መሰረታዊ ፍላጎቶችን አያሟላም።**

**የኢትዮጵያ ሕዝብ ለነጻነቱና ለመብቱ መታገል የጀመረው ዛሬ አይደለም።**

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለነጻነቱና ለመብቱ የመታገል ቆራጥነቱን አቁሞ አያውቅም። ምኞቱንና ተስፋውን፤ **ነጻነቱንና መብቱን** ተጠቅሞ፤ በድምጹ የገለጸበት ወቅት በምርጫ ዘጠና ሰባት ጊዜ ብቻ ነበር። ይህን ፍትሃዊነትና ግልጽነት የነበረውን ምርጫ ያባከነው፤ በተጻራሪው ያሸነፉትን የቅንጅት መሪዎች ወደ እስር ቤት የላከው፤ ምርጫውን ሰርቆ ሕዝቡን ተስፋ ያስቆረጠው፤ በብሄር፤ ብሄረሰብና ሕዝብ

እኩልነትና ከዚህ በሚከሰት አንድነት አመካኝቶ ፍጹም አምባገነን የሆነ የአፈና መንግሥት የመሰረተው ህወሓት ነው። ይህን ፍጹም አምባገነን መንግሥት እውቅናና አግባብነት የሰጡት ደግሞ ( a semblance of credibility and legitimacy) የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች፣ በተለይ ብአዴንና ኦህዴድ፣ የምእራብ አገሮች መንግሥታት፣ በተለይ አሜሪካኖችና እንግሊዞች እና እንደ ዓለም ባንክና እንደ አይኤም ኤፍ ያሉ አበዳሪ ድርጅቶች ናቸው።

ይህ የአፈናና የምዝበራ መንግሥት ከምርጫ ዘጠና ሰባት በኋላ ፍጹም የሆነ የበላይነት ይዞ በኢትዮጵያ ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ ብሄር ተኮር **<u>ጥላቻ ስር እንዲይዝ፣ በተለይ፣ በኦሮሞውና በአማራው ብሄረሰቦች ላይ ያነጣጠረ እልቂት እንዲካሄድ ያደረገ ስልት የተጠቀመና አሁንም የሚጠቀም፣ ድርጅታዊ ምዝበራ</u>** ተቋማዊ እንዲሆን፣ አፈናና ግድያ እንደ ተራ ነገር ተቀባይነት እንዲያገኙ ያደረገ፣ አማራውንና ኦሮሞውን "እሳት እና ጭድ" ናቸው ብሎ ሰይሞ እንዲጨራረሱ ሙከራ ያደረገና አሁንም ለማድረግ የሚሞክር፣ ወንድማማቹን የሶማሌውንና የኦሮሞውን ሕዝብ እርስ በሩስ እንዲጣላና እንዲገዳደል ያደረገ፣ በኢትዮጵያ ሕዝቦች ያለው የተለመደ ግንኙነት፣ መከባበርና አብሮ መኖር እንዲፈርስ፣ ወጣቱ ትውልድ **<u>ኢትዮጵያዊነቱን</u>** ክዶ የራሱን ብሄርና ቋንቋ እንዲቀበልና ለህወሓት አገልጋይ እንዲሆን ያደረገ አገዛዝ ነው።

በእኔ እምነት፣ ይህ አገዛዝ አገርን በዘላቂነት፣ ሕዝብን በእኩልነት ሊያስተዳድር አይችልም። ፍላጎትና ችሎታም የለውም። የአገሪቱን ባጀት እየተጠቀሙ፣ መሳሪያ እየገዙ፣ ስለላ እያካሄዱ፣ የውጭ መንግሥታትን እያባበሉ፣ የምግብ ጥገኛ ከሆነው ከኢትዮጵያ ድሃ ሕዝብ የተሰወረ፣ በአሜሪካ ብቻ፣ ለአቤቱታ (ለሎቢስቶች) **<u>በየወሩ $150,000</u>፣ <u>በየዓመቱ $1,800,000</u>** ፈሰስ የሚያደርገው አገዛዝ በሕዝብ ፍቅር አያምንም። ተወያይቶ ችግሮችን በመፍታት አያምንም። በእውነተኛ ድርድር አያምንም። ካለፉት ሃያ ስድስት ዓመታት የጭካኔ አገዛዝ ሂደት ለማጤን የሚቻለው፣ ቡድኑ፣ የሚያምነው፣ ሕዝብን እየከፋፈሉ፣ እየጨፈጨፉ፣ እያሳደዱ መግዛትን ነው። ከፋፍሎና አፍኖ መግዛት አገርን ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ከማስተዳደር ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። **<u>አፍኖ መግዛት ለሰላምና ለእውነተኛ ዲሞክራሲ አመሰራረት ጸር ነው።</u>** ዛሬ በየቀኑ ወገኖቻችን የሚሞቱበት ዋናው ምክንያት ከጠባብ ብሄርተኝነት፣ ጎጠኝነት፣ ጠባብነትና አግላይነት ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት አለው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ በተለይ ኦሮሞውና አማራው፣ ከNovember 2015 ጀምሮ እስካሁን ድረስ፣ ማለትም ለሁለት ዓመታት በተከታታይ ለሙብቱና ለነጻነቱ ሲታገል ቆይቷል። ቁጥራቸው በቅጡ የማይታወቅ፣ ሆኖም፣ በብዙ ሽህ የሚገመቱ ወገኖቻችን የባለሥልጣኑ ፓርቲ ሰለባ ሆነዋል። አስርት ሽህዎች ታስረዋል፣ እንዲሰወሩ ተደርገዋል። አሁንም ይኼው ጭካኔ እንዲቀጥል ተወስኖበታል። ይህ ቡድን ካልተወገደ ኢትዮጵያ ሰላምና እርጋታ አይኖራትም። ግድያው ይቀጥላል። አገሪቱ ያስገኘችውም መሰረተ ልማት ሊወድም ይችላል። **<u>ቀደም ሲል ዩጎስላቪያ፣ ሩዋንዳ፣ ሶማሊያና ዛሬ ሶሪያ ምሳሌዎች ናቸው።</u>**

ህወሓት ከወር በላይ የዝግ ችሎት ሲያካሂድ ምናልባት ራሱን ተችቶ፣ የብሄር ነጻ አውጭ ግንባርነቱን ስም ትቶ፣ **<u>የኢትዮጵያ ሕዝብ የስልጣኑ ባለቤት የመሆን</u>** መብት አለው ብሎ፣ አዲስ ምእራፍ ይከፍት ይሆን የሚል የሚል ጥያቄ አስተናግድ ነበር። አልሆነም። "ነብር ቀለሙን አይለውጥም" እንዲሉ፣ ህወሓት ራሱን አይለውጥም። እንዲያውም መቀሌ የተካሄደው ዝግ ችሎት ያስከተለው ውጤት ከበፊቱ የባሰ ይሆናል የሚሉ ብዙ ታዛቢዎች አሉ። ኢህአዴግ ካለፉት ውድቀቶች አልተማረም፣ የተከተለው የህወሓትን ስልት ነው።

ህወሓት የመንደር ቡድን ሆኗል። ይህ የመንደር ቡድን ከበፊቱ በባሰ ሁኔታ ራሱን በደህንነት፣ በልዩ ኃይል፣ በመከላከያ፣ በስለላና በውጭ ግንኙነት ዘርፎች አጠናክሮ አሁንም የበላይነቱን ይዞ አፈናውን፣ ግድያውንና የኢኮኖሚ የበላይነቱን፣ ድርጅታዊ ምዝበራውን ለመቀጠል ወስኗል። የችግሩ እምብርት ይኼው ነው። ችግሩ አገር አቀፍ ሆኗል።

ዛሬ ኢትዮጵያ የደረሰችበት ደረጃ ከመቸውም በላይ የሚያሳስብ፣ ኢትዮጵያን ለባሰ አደጋ የሚያጋልጥ፣ አገሪቱ እንድትበታተን የሚያመቻችና ወደ የእርስ በርስ ጦርነትና እልቂት የሚያመራ ሆኖ ይታያል።

ይህን የምልባቸውን አስኳል ምክንያቶች ከዚህ በታች አቀርባለሁ፣

1. በአዲግራት ከተማ የሚማሩ የአማራ፣ የኦሮሞና ሌሎች የትግራይ ብሄር አባል ያልሆኑ የኮሌጅ ተማሪዎች መገደላቸው፣ የቀሩት ተማሪዎች ወደየቤታቸው፣ ወደ ክልላቸው እንዳይመለሱ በህወሓት መከልከላቸው፣
2. ህወሓት ኮሌጆችን፣ ዩንበርስቲዎችን በፌደራል ፖሊስ፣ በአጋዚና በሌሎች ኃይሎች ከቦ የሚያካሂደው አፈናና የፍራቻ ዛቻ፣ አደገኛ መሆኑ፣ ከወጣቱ ትውልድ ጋር ጥላቻን መፍጠሩ፣
3. ይህ ብሄር ተኮር (**<u>Targeted and Selective Killing</u>**) ግድያና አፈና መላውን የአማራውንና የኦሮሞውን ተማሪና ሕዝብ ማስቆጣቱ፣ ህወሓት ኃላፊነት ለመውሰድ አለመፍቀዱ፣
4. አዲሱ የህወሓት አመራር ሆነ ብሎ፣ **<u>"በትግራይ ሕዝብ ላይ"</u>** ጭፍጨፋ ሊካሄድበት ነው ብሎ የትግራይን ሕዝብ ከሌላው ወንድም፣ እህቱ ሕዝብ ለይቶ መቀስቀሱና ማስተጋባቱ፣
5. ጊዜና ጥረት ቢጠይቅም፣ በንጹህ የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የተካሄደውና አሁንም የሚካሄደው ጭካኔ፣ አፈናና ግድያ ባለሥልጣናትን በኃላፊነት እንደሚያስጠይቃቸው ግንዛቤ ላይ መደረሱ፣
6. ይህ ብሄርን ከብሄር የመለየት ዘዴና ስልት፣ ከዚህ በፊት በጎንደርና በሌሎች አካባቢዎች ሕዝባዊ አመጽ ሲነሳም ህወሓት፣ ተመሳሳይ የፈጠራ ወሬ አስወርቶ መክሸፉ፣ ሆኖሞ፣ ይኼን የሃሰት መፈክር አገር አቀፍ በሆነ ደረጃ ለማስተጋባት መሞከሩ፣

ጎንደሬው “የኦሮሞ ደም ደማችን ነው” ያለውና በተመሳሳይ፤ የኦሮሞው ሕዝብ “የወልቃይት ጥያቄ የእኛም ነው፤ የኦሮሞ ወጣት “አባይ ኬኛ” ማለቱ ለህወሓት ስጋት መፍጠሩ። የኦህዴድ አመራር፤ አባቶች፤ ቄሮዎች ወደ ባህር ዳር ሄደው የኦሮሞውንና የአማራውን ሕዝብ ጥንታዊ ግንኙነት፤ ወንድማማች/እህትማማችነትና ፍቅር ማስተጋባታቸው። የኢትዮጵያ ጥንታዊ ታሪክ ይኼን ጠንካራ ግንኙነት ያሰመረበት መሆኑ ቀስ በቀስ እውቅና ማግኘቱ በህወሓት ውስጥ ፍራቻን ማስከተሉ ሊጠቀሱ ይገባል። ይህ ግንኙነት እንዲስፋፋ ሁላችንም ጥረት ማድረግ አለብን።

7. ከዚህ ላይ ታሪክ የሚያስታውሰው፤ ወጣቱ ትውልድ ሊቀበለው የሚገባው አስኳል ጉዳይ አለ። ይኼውም፤ አጼ ቴዎድሮስ ለኢትዮጵያ አንድነት ሲታገሉ ሕዝቡንና የሕዝቡን አንድነት መሰረት ማድረጋቸው ነው። የእንግሊዙ ጋዜጠኛ Henry Morton Stanley, Kunasina/Meqdela በተባለው መጽሃፉ አጼ ቴዎድሮስ የተናገሩትን እንዲህ ብሎ ጠቅሶታል። “ኦርሞና አማራን በአንድ ሰደቃ (መአድ) ያላበላሁ እንደሆነ፤ እኔ የክርስቶስ ባሪያ፤ የቅዱስ ዮሃንስ እለት (ለት) ክርስቲያን አትበሉኝ።” ይህ ታሪካዊ መርህ በአዲሱ ትውልድ ተቀባይነት ማግኘት፤
8. በአንድ “ሰደቃ” የሚበላ ሕዝብ ወንድማማች፤ እህትማማች መሆኑን አሰመሩበት ማለት ነው። ኦሮሞውና አማራው የኢትዮጵያ ምሰሶዎች ናቸው የምልበት ምክንያትም ይኼው ነው። ምሰሶ የሆነ ሕዝብ ሌላውን ወንድሙን፤ እህቱን ለይቶ አይገድልም፤ አያጠቃም፤ ከሚኖርበት መሬት አያባርርም። የኢትዮጵያዊነት ትርጉም ይኼው ነው።
9. የአማራውና የኦሮሞው ሕዝብ ህወሓትንና የትግራይን ሕዝብ የመለየት ችሎታውን በተከታታይ አስመስክሮ፤ ግን ህወሓት ለመቀበል አልቻለም ማለቱ፤
10. ችግሮችን በመወያየት፤ በሰላምና በድርድር ለመፍታት ያልቻለውና የማይፈልገው ህወሓት አሁን ሆነ ብሎ የያዘው ስልት የሌሎች ብሄሮችን፤ ለምሳሌ የሶማሌን፤ የአፏክን ታማኝ ግለሰቦችና ቡድኖች እየመለመለና እያስታጠቀ በሌላው፤ በተለይ፤ በአማራውና በኦሮሞው ሕዝብ ላይ እንዲነሳ መቀስቀሱ፤
11. ኦሮሞውና አማራው “ሊነሳብህ ነው፤” ይኼ ለእኛ አደጋ ነው የሚል በጣም የሚያሳዝንና የሚያስፈራ ፕሮፓጋንዳ መነዛቱና ይህ የህወሓት የሃሰት ለፈፋ ልክ የሩዋንዳ አይነት እልቂት እንዲካሄድ የሚያደርግ ሁኔታን መፍጠሩ፤
12. ህወሓት ቢችል ኢህአዴግን ለራሱ በሚፈልገው ግብ መሰረት፤ ታማኞችን መልምሎ እንደገና ማቀናጀት፤ ባይቻል ግን የራሱን **<u>የደህንነት፤ የስለላና የመከላከያ ኃይል</u>** አጠናክሮ “መፈንቅለ መንግሥት” ለማካሄድና ወታደራዊ መሰል አገዛዝ ለመመስረት የወሰነ መሆኑ፤
13. ኢህአዴግን እንደ ገና ማጠናከር ያስፈልጋል የሚለው ስልት የህወሓት አጀንዳ ነው። ይህ አጀንዳ ስኬታማ ሊሆን የሚችለው የአባል ድርጅቶችን እንደ ገና በማዋቀርን፤ ለመሰረታዊ ለውጥ የሚታገሉትን በማስወገድና በማግለል መሆኑ “የአደባባይ ምስጢር ነው” እያለ ሕዝቡ ማስተጋባቱ፤
14. ይህን ሲያደርግ ህወሓት የሚነግድበት አዲስ ስልት “የብሄር አደረጃጀትና አመራር” አያዋጣም በሚል መልኩ በመጠቀም፤ ለለውጥ የሚታገሉትን፤ በተለይ **<u>የኦሮሞውንና የአማራውን</u>** ብሄረሰቦች ተስፋ የሚሰጡ ግለሰቦችን ለማፈን፤ ለማሳደድ፤ ለመግደል ወዘተርፈ የተዘጋጀ መሆኑ፤
15. ባለፉት ወራቶች በተከታታይ፤ በኦሮሞያና በአማራው ክልሎች በተከታታይ የሚካሄዱት በወጣቶች መሪነት የሚደረጉት ትግሎች ስር ነቀል የሆነ አገዛዝ አስፈላጊ ነው፤ **<u>“የወያኔ አገዛዝ በቃን”</u>** የሚሉ መፈክሮችን ያዘለ መሆኑ ለህወሓት የበላይነት አደጋ የሚያስከትል መሆኑ፤
16. ይህን ቀና አስተሳሰብና አቅጣጫ ከማበቡ በፊት ለመደምሰስ፤ ህወሓት “ከራሱ አብራክ” የፈጠራቸውን ተላላኪዎችና ታዛዢዎች፤ ለምሳሌ፤ የአማራውን ሕዝብ ያዋረደውን፤ የህወሓትን ካድሬ አለምነህ መኮነንን ተተኪ ለማድረግ መሞከሩ፤ በኦህዴድም በኩል ታማኝ የሆኑ የኦሮሞ ብሄር አባላትን ለመመልመልና ድርጅቱን በበላይነት እንዲመርሩ ሙከራ እየተድረገ መሆኑ፤
17. ህወሓት የለመደው የከፋፍለህ ግዛው ስልት አንዱን ብሄር ከሌላው ጋር ማናከስና ማጋጨት ስለሆነ፤ ዛሬ በሚዘገንን ደረጃ፤ የሶማሌ ክልል አጋሮቹን/መሰሎቹን “ልዩ ኃይል” በሚል ስያሜ፤ እስከ አፍንጫው አስታጥቆ፤ ከዚህ በፊት በመልካም ጉርብትናና በሰላም ጎን ለጎን ይኖሩ በነበሩት ወንድማማች/እህትማማች ኢትዮጵያዊያን መካከል የእርስ በርስ ጦርነት እንዲካሄድ ማድረጉ፤
18. የህወሓት ፌደራል ፖሊስ፤ አጋዚና ሌላ ኃይሎች ተባብረው ቅሊንጦ በሚኖሩ አስራ ስድስት ንጹህ በሆኑ፤ የኦሮሞ ኢትዮጵያዊያን ላይ ጭፍጨፋ ማካሄዱ፤ ይህ ጭፍጨፋ የኦሮሞውን ሕዝብ ብቻ ሳይሆን መላውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ማሳዘነ፤ መቀስቀሱ፤
19. **<u>የኦህዴድና የብአዴን አመራሮች</u>** ለዚህ አስከፊ እልቂት ተቆርቋሪ እንዲሆኑ፤ የጀመሩትን መቀራረብና በኢትዮጵያዊነት መንፍስ የሚያደርጉትን አንድነት እንዲገፉበት ጫናና ተጨማሪ ግብአት መሆኑ፤
20. በንጹህ የኦሮሞው ሕዝብ ላይ የሚደረገው ተከታታይ አይን ያወጣ ጭፍጨፋ አሁንም መቀጠሉ፤ December 12 በአስራ ስድስት፤ ከDecember 14 ጀምሮ እስከ December 18 ባለው ጊዜ ብቻ በስድሳ አንድ ኦሮሞ ኢትዮጵያዊያን ላይ ጭፍጨፋ እንደተካሄደ ሮይተርስ፤ ቢቢሲና የአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ መዘገባቸው፤
21. በተመሳሳይ፤ ከአምሳ ያላነሱ ሶማሌ ኢትዮጵያዊያንም መገለደላቸው ይፋ መሆኑ፤

22. Washington Post, December 19, 2017 ሰብሰብ አድርጎ ባወጣው ዘገባ መሰረት፤ **ቢያንስ "61** የኦሮሞ" ወገኖቻችን መገደላቸው፤ "2015 and 2016" የተካሄደው ሕዝባዊ አመጽና እምቢተኛነት ለብዙ ወገኖቻችን እልቂትና በግልጽ ለሚታየው "Increasing Instability" ችግር መሰረት ወይንም ምክንያት መሆኑ፤
23. ችግሩ ስላልተፈታ ባለፈው ሳምንት "**29 ethnic Oromos** killed by ethnic Somalis in the region's Hawi Gudina and Daro Lebu districts." ይህን እልቂት ተከትሎ "This triggered revenge attacks by Oromos, resulting in the deaths **of 32 Somalis."** ይህ መሰረታዊ ችግር እየተባባሰ መሄዱ፤
24. የኢትዮጵያ ገዢዎች ችግሮችን በመፍታት ፋንታ፤ ለስልጣንና ለጥቅም ብቻ በመቆም፤ ሰላማዊ ሰልፎችን ለማፈን የግድያ እርምጃዎችን በተከታታይ ማካሄዳቸው ሁኔታውን ማባባሱ። ከላይ የጠቀስኩት ጋዜጣ እንዲህ በሚል አስቀምጦታል። "The cause of the latest violence ....followed protests in **Oromia's Celenko town** where **16 ethnic Oromos** were killed last Tuesday, December 12, 2017 by troops (Federal and security) trying to disperse the crowd." እነዚህ ንጹህ ወገኖቻችን በገዢዎቹ ትእዛዝ መገደላቸው ከጀርባ ሆነው ሁኔታውን ለማባባስና የእርስ በርስ ጦርነት እንዲካሄድ የሚፈልጉ ኃይሎች መኖራቸውን ማሳያቱ፤
25. ይህ የእልቂት ዑድት (Cycle) በተደጋጋሚና በተከታታት በአማራው ብሄር አባላት ላይ መካሄዱን ታሪክ መመዝገቡ፤ በአፏኩ ሕዝብ ላይም የተደረገው ጭፍጨፋ ተመሳሳይ እልቂት መሆኑ፤
26. የኢትዮጵያ **ምሰሶዎች በሆኑት በኦሮሞውና በአማራው** ሕዝብ ላይ እንደዚህ ያለ ጭካኔ የሚያካሂደው በውጭ ጠላት አለመሆኑ ሰፊ እውቅና ማግኘቱ፤
27. እነዚህ ሁሉ ብሄር ተኮር ጭፍጨፋዎች በዓለም ሕግ ሊያስከስሱ የሚችሉ መሆናቸው ግንዛቤ ማግኘታቸው፤
28. ብሄር ተኮር ጭፍጨፋው ተደማምሮ ሲታይ፤ የጣሊያን ፋሽስት ወረራ ከተካሄደ ወዲህ እንደዚህ ያለ የተቀነባበረና የማይበርድ፤ የጭካኔ ዘመቻ የተካሄደውና አሁንም የሚካሄደው በአሁኑ በህወሓት የበላይነት በሚሽከረከረው አገዛዝ መሆኑን የኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን መላው የዓለም ሕዝብ እየተቸው መገኘቱ፤
29. ይህ ብሄር ተኮር ግጭት፤ አፈናና ጭፍጨፋ በአስቸኳይ ካልቆመ ለኢትዮጵያ መፈራረስና ለእርስ በርስ እልቂት (Genocide) መሰረት መሆናቸውና፤
30. ለዚህ አደጋ በኃላፊነት የሚጠየቁት ዛሬ ኢትዮጵያን የሚገዙት ባለሥልጣናት፤ በተለይ ህወሓት መሆኑ መታወቁ።

ህወሓት አሁንም የሚከተለው **ራእይና ተልእኮ፤** የተመሰረተበትን የአማራ ብሄር ጥላቻ ማኒፌስቶውን ነው። ይህ የብሄር ጥላቻ ዛሬ ስር ሰዶ ኦሮሞውንና አማራውን የእልቂት ኢላማ አድርጓቸዋል። አበው እንደሚሉት፤ "እያ ጅቡ፤ ጅቡ ሳታመኻኝ ብላኝ" ነውና ህወሓት የሚፈጥራቸው ሌሎች ምክንያቶች ምንም ፋይዳ የላቸውም። ሁለቱን ብሄሮች በአንድ ላይ ጨፍልቆ እንዲገዙ ማድረግ ወሳኝ መሆኑን የተገነዘበ ቡድን ነው። ሕዝብ ድንጋይ አይደለም፤ ህያው ነው። ህያው ስለሆነ ግፍን አይቀበልም። ራሱን ከእልቂት የማዳን መብት አለው።

ለዚህ የሚያዋጣው፤ ቢቻል ሁሉም ኢትዮጵያዊያን ከጎሳ፤ ከኃይማኖትና ከግል ጥቅም ባሻገር **ኢትዮጵያንና የኢትዮጵያን** ሕዝብ ማስቀደም፤ ተባብሮ አፋኙን ቡድን በሕዝባዊ አመጽ ለድርድር ፈቃደኛ እንዲሆን ማስገደድ ነው።

ለዚህ የሚረዳው የፖለቲካ ሂደት **አህዴድና ብአዴን** በባህር ዳር የጀመሩትን ሕዝብን ከሕዝብ ጋር የማገናኘት፤ የማቀራረብና የማፋቀር ጉዟቸውን ከፍ አድርገው የፖለቲካ አንድነት ለመፍጠር መሞከርና ከሌሎች አገር ውስጥና ከአገር ውጭ ካሉ አገር ወዳድና ዲሞክራሳዊ ኃይሎች ጋር ግንኙነት መፍጠር ነው። **ኢትዮጵያዊነትን** አንግበው የኢትዮጵያ **ሕዝብ የፖለቲካው** ስልጣን ባለቤት እንዲሆን ቆራጥነትና ጀግንነት ማሳየት ነው።

ከአሁን በኋላ ህወሓት የበለይነቱን ይዞ የሚገዛበት ምንም ምክንያት የለም። ሊገዛ የሚችለው በራሱ ጥንካሬ ሳይሆን በሌሎቻችን ደካማነት፤ በራሳችን መከፋፈል፤ በሌሎቻችን የስልጣን ሆነ የንዋይ ስግብግብነት፤ በሌሎቻችን ፈሪነት፤ በሌሎቻችን ተላላኪነት ወዘተርፈ ይሆናል።

ህወሓት ጨቋኝነቱን፤ ጨካኝነቱን፤ ጠባብ ዘረኛነቱን፤ መንደረኛነቱን፤ ጸረ-ሕዝብ፤ ጸረ-ዲሞክራሲና ጸረ-ሰላማዊነቱን በተደጋጋሚ ለሃያ ስድስት ዓመታት አሳይቷል። ህወሓት ዛሬ የሚደራደረው፤ ለይስሟል ተቃዋሚ ናቸው ከሚላቸው ራሱ ከፈጠራቸው አጎብዳጆችና ፕሮፌሰር አስራት "ሆዳሞች" ብለው ከሰየሚቸው ጋር ብቻ ነው።

እነዚህ ቡድኖች የሚደራደሩት ራሳቸውን ለማገልገል ከሚያስችላቸው ክወንበር ይገባኛልነት ጋር ነው። ህወሓት ሃያ ሁለት ፓርቲዎች ጋር እደራደራለሁ ሲል፤ እነዚህ ፓርቲዎች ለምን ብሄራዊ ራእይ፤ ተልእኮና የአገዛዝ አማራጭ ቆመዋል ብለን የመጠየቅ ሃላፊነት አለብን። እነዚህ "ተቃዋሚ ነን" ባዮች ጠባብ ብሄርተኝነት ለኢትዮጵያ አያዋጣትም፤ አንቀጽ ሰላሳ ዘጠኝ አገራችን እያፈራረሳት ነው፤ ሕዝባችን እርስ በርሱ እንዲገዳደል እያደረገው ነው አላሉም። ቃል ኪዳን የገቡት ለህወሓት ነው፤ ለኢትዮጵያና ለኢትዮጵያ ሕዝብ አይደለም። አዲሱ የኢህአዴግ መግለጫ ያጠናከረው ሂደት ተመሳሳይ ነው።

በብሄር ወይንም በነገድ ልዩነቶች ላይ የተመሰረተው ስርዓት አክትሞለታል። አያዋጣም። አያዋጣም የምልበት መሰረታዊ ምክንያት፤ በአማራው ክልል ሕዝብን ከሕዝብ ጋር አጋጭቶታል፤ አማራውን ከትግራዩ ጋር አጋጭቶታል። በምስራቅና በደቡብ ኦሮሞውን

ከሶማሌው ጋር አናክሶታል፤ ደም እየፈሰሰ ነው። የዘርን ፖለቲካ ሕዝቡ አውግዞታል። የተወገዘን አገዛዝ መልሶ ለማቋቋም አይቻልም። ይህን ለማድረግ የሚቻለው በንጹህ ሕዝብ ላይ እልቂትን በማካሄድ ብቻ ይሆናል ማለት ነው። ይኼ ሶማሊያን፤ ደቡብ ሱዳንን፤ ሶሪያን ወደ መሰለ አደገኛ መንገድ ያመራል።

የኦህዴዱ ዶር አቢይ አህመድ ብዙ ቁም ነገሮችን ተናግሯል። “ያለን አማራጭ ሁለት ነው፤ አንዱ በአንድነት ሆነን መታገል፤ ሌላው እርስ በርሳችን መጠፋፋት ነው፤ እኔ የመጀመሪያውን እመርጣለሁ” ያለው። ሁለተኛው አንድ ወጣት ልጅ ያለውን ጠቅሶ “አማራውና ኦሮሞው ልክ እንደ ጥቁር ድንጋይ ነው። ጥቁር ድንጋይን በመዶሻ ብትመታው አይሞትም፤ ራስክን መልሶ ይመታሃል፤ ኦሮሞውና አማራው ጠንካራ ነው፤ አይሞትም” ያለው።

ይህ የኢትዮጵያ ምሰሶ የሆነው የኦሮሞና የአማራ ሕዝብ ጭፍጨፋና ጭካኔ ቢደርስበትም አይሞትም። የኢትዮጵያ ሁለት ሶስተኛ የሚገመት ሕዝብ በምንም ሊሞት አይችልም። ወድቆ ይነሳል፤ ጠንካራ ሆኖ፤ ተባብሮ አገሩን ይታደጋታል።

በሌላ በኩል፤ በነገድ፤ በብሄር ልዩነቶችና ጥላቻዎች ላይ የተመሰረተው የህወሓት አገዛዝ አደገኛ ስለሆነ አያዋጣም። ትላንት በአማራው ላይ፤ ዛሬ በኦሮሞው ላይ፤ ነገ በሌላው ላይ ጭካኔ እያካሄደ ሊቀጥል አይችልም። የአገዛዝ ለውጥ ያስፈልጋል። ይኽ አስፈላጊና ወሳኝ ለውጥ መሰረት ሊይዝ የሚችለው አፋኙን ቡድን ከስልጣን በማውረድና አማራጭ በማቅረብ ብቻ ነው።

ለውጥ ለምን ያስፈልጋል የሚለው የተመለሰ ይመስለኛል፤

- በሕዝብ ላይ የሚካሄደው ጭካኔና ጭፍጨፋ እንዲቆም ለማድረግ፤
- ሁሉን ባለድርሻዎች የሚያሳትፍ **<u>ብሄራዊ የሆነ፤ የአንድነት የሽግግር መንግሥት</u>** ለመመስረት እንዲቻል፤
- እንደ 1991 የለንደኑ አይነት ድርድር፤ ማለትም፤ **<u>አገር ወዳዶችንና ዲሞክራቶችን ያላሳተፈ፤ እንዲያውም ያገለለ ውይይትና ድርድር እንዳይደገም ለማድረግ፤</u>**
- ለዚህ አስፈላጊ የሽግግር ሂደት የሚስማሙትን፤ በአገር ቤትና በውጭ ያሉትን የፖለቲካ ድርጅቶችን አስቀድሞ ማነጋገርና በአንድ ብሄራዊ አላማ ላይ እንዲስማሙ ለማመቻቸት፤
- በኢትዮጵያ የአስተዳደር ክፍተት እንዳይኖር ቅድመ ዝግጅቶች እንዲደረጉ አስቀድሞ እቅድ እንዲኖር ለማመቻቸት፤
- በአገሪቱ ዘላቂ ብሄራዊ መግባባት፤ እርቅና ሰላም እንዲሰፍን ለማመቻቸት፤
- ይህ ብሄራዊ መግባባትና የሽግግር መንግሥት ገዢውን ፓርቲም እንዲያካትት ለማመቻቸት፤
- በተወሰነ ጊዜ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ተካሂዶ **<u>ሕዝቡ የፖለቲካ ስልጣኑ ባለቤት</u>** እንዲሆን ለማድረግ፤
- ብዙ መስዋእት የተከፈለባት የኢትዮጵያ ነጻነት፤ ብሄራዊ አንድነትና ሉዐላዊነት አስተማማኝ መሰረት እንዲኖረውና ኢትዮጵያ በጣላቶቿም ሆነ በወዳጆቹ መንግሥታት እንድትከበር ለማድረግ፤
- በአሜሪካኖች ድጋፍ ስልጣን የያዘው ህወሓት እስካሁን ስልጣን ይዞ የቆየበት ሁኔታ የተለወጠ መሆኑንና አማራጭ ሊገኝ መቻሉን እውቅና እንዲኖረው ለማድረግ፤
- ከሕዝብ አብራክ የተወጣጣው ተራው የኢትዮጵያ የመከላከያ “ኃይል” አባላት ለእናቶቹ፤ ለአባቶቹ፤ ለቤተሰቡ፤ በተለይ ለልጆቹና ለእናት አገሩ በማሰብ አፋኙን ህወሓትን ወደ ጎን ትቶ ከሕዝቡ ጋር አብሮ እንዲቆም ለመቀስቀስና ዳር ድንበሩን እንዲከላከል ቅስቀሳዎችን ለማድረግና፤
- ከአሁን በኋላ ወታደሩ በራሱ ወገኖች ላይ ግድያ እንዳይፈጽም አደራ ለማለት።

ለማጠቃለል፤ እኛ ኢትዮጵያዊያን ከአሁን በኋላ ያለን አማራጭ አንድ ብቻ ነው። ይኼውም፤ ጠባብ ብሄርተኛነትን አስወግደን፤ የኢትዮጵያን **<u>ግዛታዊ አንድነትና ሉዐላዊነት ተቀብለን፤</u>** ሁሉንም ኢትዮጵያዊያን የሚያስተናግድ፤ በሕግ የበላነት፤ በዜግነትና በኢትዮጵያዊነት እሴቶች ላይ የተመሰረተ ዲሞክራሳዊ አገዛዝ እንዲመሰረት ያልተቆጠበ ጥረት ማድረግ ብቻ ነው። የሕዝብን ስልጣን ያልተቀበለ ቡድን በኢትዮጵያ ሚና ሊኖረው አይገባም።

በምንም መስፈርት ልንክደው የማንችለው ክስተት፤ በህወሓትና በኢትዮጵያ ሕዝብ መካከል የተከሰተው ተቃርኖ እየተስፋፋ መሄዱን ነው። ህወሓት ለሃያ ስድስት ዓመታት ሲቀማ፤ ሲበላ፤ ሲያሰቃይ ቆይቶ አሁንም ልግዛና ልብላ ብሎ ራሱን አድሏል። የኢትዮጵያን ሕዝብ የነጻነት፤ የእኩልነት፤ የፍትህ፤ የስራ እድል ማግኘት፤ የብሄር መግባባት፤ የዲሞክራሲና ሌሎች አስኳል ግዳዮችን ንቆ ወደ ጎን ትቷቸዋል። ሕዝብን ካገለለና ከናቀ የመግዛት አግባብነት ሊኖረው አይችልም።

ስለሆነም፤ በአሁኑ ወቅት ሕዝብን የናቀው፤ ህወሓት፤ በተቀነባበረ ሁኔታ የሚያካሂደውን ግድያና እልቂት ማውገዝና ከሕዝቡ ጎን መሰለፍ የእያንዳንዱ አገር ወዳድና ዲሞክራት ሃላፊነት ነው። ይህ ሃላፊነት ብሄር አይለይም።

ኢህአዴግ የኢትዮጵያን ሕዝብ ደጋግሞ ይቅርታ መጠየቁ አግባብ አለው። ከዚህ በላይ ግን መሰረታዊ ችግሮችን አልነካቸውም። ሊነካቸውም አይችልም። ሕዝቡ እንዳይዘናጋ ማድረግ የሌሎቻችን ኃላፊነት ጭምር ነው።

***<u>ፊት ለፊት ሆነው የሚከራከሩት ብአዴንና ኦህዴድ</u>*** ከአሁን በኋላ ከህወሓት ጋር ያላቸው ቅራኔ በቀላሉ አይፈታም። ምክንያቱም የንጹሃን ደም ፈሷል፤ እየፈሰሰ ነው። ያላቸው አማራጭ ከሕዝብ ጎን መቆም ነው።

ከሕዝብ ጎን ከቆሙ ማንም ኃይል አያሸንፋቸውም። ከሕዝብ ጎን ከቆሙ ለሕዝብ ስልጣን፤ ለፍትህ-ለርትእ፤ ለሕዝባዊ አንድነት ተባብረውና ደፍረው መቆም ታሪካዊ ግዴታቸው ነው። ይኼው ነው ከአፋኙና ከጠባብ ብሄርተኛው ቡድን የሚለያቸው።

የትግራይ ሕዝብም ታሪካዊ ግዴታውን ሊወጣ የሚችለው ሌላውን ሕዝብ በመጥላትና በመጠራጠር አይደለም። ከሌላው ሕዝብ ጋር አንድነት በመፍጠር ነው። ይህ ደግሞ ህወሓት አለመለወጡን መቀበልን ይጠይቃል። አለመለወጡን ከእኔ በበለጠ የሚያውቁት የትግራይ ተወላጆች ናቸው።

ለምሳሌ፤ አቶ ገብሩ አስራት በቪኦኤ እንደተናገረው፤ በአዲስ የተዋቀረው ህወሓት "ምንም አይነት ዲሞክራሳዊ ለውጥ ሊያመጣ አይችልም።" ፕሮፌሰር መረራ ጉዲናንን "ሽብርተኛ ነህ፤ አሬናን ጠላት ነህ" ብሎ የፈረጀ ቡድን በምንም ዲሞክራሳዊ ሊሆን አይችልም።

ህወሓት/ኢህአዴግ አሁንም፤ ማንኛውም በህብረ-ብሄር ሆነ በብሄር የተደራጀ ተቀናቃኝ ወይንም ተቃዋሚ ነኝ የሚል የፖለቲካ ፓርቲ የተፈረጀውና የሚፈረጀው በጠላትነት ነው። ለሕዝብ ደህንነት የቆመም ፓለቲካ ፓርቲ የሚፈረጀው በተመሳሳይ መስፈርት ነው፤ በኢህአዴግ ያሉትን ብአዴንና ኦህዴድን ጨምሮ።

"ወይ ባልዘፈንሽ፤ ከዘፈንሽ ባላሳፈርሽ" እንዲሉ እነዚህ ሁለት ድርጅቶች ለሕዝባችን እልቂት እኛም ተጠያቂዎች ነን ብለው ከጀመሩ ያላቸው አማራጭ ራሳቸውን ከህወሓት መንጋጋ ነጻ ማውጣት ነው።

ኢትዮጵያ **ለዘላለም**